# ዶ/ር ነጋሦ ፣ ዶ/ር ፀጋየ አራርሳ፣ ሰንደቅ ዓላማ፣ሕገ-መንግሥት… ይነጋል በላቸው

July 11, 2018




ወቅታዊ ጉዳዮቻችን እጅግ ብዙ ናቸው፡፡ ከዚህም ከዚያም እያልኩ የተሰማኝን ጥቂት ልበል፡፡ ሰሚ ካገኘሁ እሰዬው፡፡ ባላገኝም እምብዛም አልከፋም፡፡ ጊዜና ፈጣሪ በርካታ ጥያቄዎቼን መልሰውልኛልና በሰዎች መስማት አለመስማት መቸገር ከንቱ እንደሆነ ተረድቻለሁ፡፡

ጠ/ሚ ዶ/ር ዐቢይ አህመድን ወደ ፖለቲካው መድረክ አውጥቶ ይህን ሁሉ ተዓምር ያሠራው ሰው ሣይሆን ፈጣሪያችን መሆኑን የሚክድ አይኖርም ብዬ አምናለሁ – ሁሉም ሰው የሚለውም እንደዚህ ነው፡፡ የዘመናት የሕዝብና የሀገር ዕንባ አምጦ የወለደውን ይህን ሮጦ ያልጠገበ ብላቴና “በኔ ትግልና መስዋዕትነት ነው ያመጣሁት!” ብሎ የሚታበይ አካል ወይ ግለሰብ ካለ ትልቅ ስህተት ነው፡፡ ምክንያት መሆን ግን ይቻላል፡፡ ቄሮ ምክንያት ነው፤ ፋኖ ምክንያት ነው፤ የሬቻ በዓል ዕልቂት መነሻ ነው፤ የጎንደሩ የኮሎኔል ደመቀ ዘውዱ ጀግንነት እርሾ ነው፡፡ አለምክንያት ውጤት አይመዘገብም፡፡ ዋናው ግን የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ነው፡፡ ስለዚህ በድል ክፍፍል ሰዎች ሊናቆሩ እንደማይገባ ማስታወስ አስፈላጊ ነው፡፡ ደግሞም ድሉ ጀመረ እንጂ ከግማሽ መንገድ እንኳን ገና ፈቀቅ አላለም፡፡ በተበዮች መካከል ስምምነትና ፍቅር ከጠፋ ደግሞ የጭራቆቹ መንግሥት ተመልሶ እንደሚመጣና የከፋ አገዛዝ ሊቀጥል እንደሚችል ሁሉም ሊረዳ ይገባል፡፡መታበይ የውድቀት መንስኤ ነውና፡፡

ልዩነት ጥሩ ነው፡፡ ልዩነትን ማክበር ተገቢ ነው፡፡ አንዳንድ ልዩነቶች ግን የሠራነውን ሁሉ እስኪያፈራርሱ ድረስ ሲያድጉ ዝም ማለት በተለይ በቅጡ ባላደጉ የኛን መሰል ሀገሮች ውስጥ አግባብ አይደለም፡፡ በስመ “ልዩነት ወርቅ ነው” እርስ በርስ በሚጠፋፉ ሃሳቦችና አመለካከቶች የተነሣ ሕዝባችን ሊቆራቆስና ለተጨማሪ ክፍፍል ሊዳረግ አይገባም፡፡ የታዋቂ ሰዎችና የምሁራን አንደበት ደግሞ እሳት ነው፡፡ ይፋጃል፤ ያፋጃል፡፡ ስለዚህ ቆም ብለን መተያየት አለብን፡፡ ሁሉም ለሚያልፍ ነገር የማያልፍ ጠባሳ በሀገራችንና በሕዝባችን ላይ መጣል የለብንም፡፡

ሰሞኑን ዶክተር ነጋሦ ጊዳዳን ምን እንደነካቸው ማወቅ አልቻልኩም፡፡ ወጣቶቹ እነ ዶ/ር ፀጋየና ዶ/ር ሄኖክ በዕድሜም ሆነ በተሞክሮ ብዙም ባለመብሰላቸው ያልተከሉት ዱባ በፈጠረባቸው ጥጋብ ቢዘሉ

አይፈረድባቸውም፤ ጥግ ሆኖ በሰው ስቃይ መዝናናትና መፈላሰፍ ለማንም የሚከብድ አይደለም፡፡ ዶክተር ነጋሦ ግን ብዙ ያውቃሉ ሲባል አድሮ ቃሪ መሆናቸው ያሳዝናል፡፡ ለቃል አጠቃቀሜ ይቅርታ ይደረግልኝና እኚህ የማከብራቸው ሰው ጃጅተዋል ወይም ከዘር ፖለቲካው ስካርና ከጎሣኝነት ምርቃና ገና አልወጡም፡፡ "ካረጁ አይበጁ" ይባልስ የለ?

"የባህር ዳሩ ሠልፍ ሕገ መንግሥት የጣሰ ነው" ማለታቸውን ከተለያዩ የሚዲያ አውታሮች አነበብኩ፡፡ በዚሁ ውልየለሽ አነጋገራቸው ላይ የተጻፉ ትችቶችንም ዳሰስኩ፡፡ የራሴን ጥቂት ቃላት መስጠት አለብኝ ብዬም ብዕሬን አነሣሁ፡፡ ካለመናገር መናገር ይሻላልና፡፡

ዶ/ር ነጋሦ የሚያደምጡኝ ከሆነ – የኢትዮጵያ ሕዝብ እየታገለ ያለው "ሕገ መንግሥትም፣ መንግሥትም፣ መከላከያም፣ ፖሊስም፣ ዳኛም፣ ፍርድ ቤትም፣ አገርም…የለኝም" ብሎ ነው፡፡ ሕገ መንግሥት ቢኖረውማ ለምን ሰልፍ ይወጣል? ሕገ መንግሥት ያላቸው ሀገሮች ሕዝቦች ለተለያዩ ችግሮቻቸው ሠላማዊ ሠልፍ አይወጡም ማለቴ አይደለም፤ ይወጣሉ፡፡ እኛ ኢትዮጵያውን ግን በተለይ ከግንቦት 20 1983 ዓ.ም ጀምሮ የአጭበርባሪዎችና የወሮበሎች ቡድን አፓርታዳዊ የሽፍታ መንግሥት እንጂ ዶ/ር ነጋሦ ጥብቅና ሊቆሙለት የሚገባው የሕዝብ ሕገ መንግሥት አልነበረንም፡፡ እርሳቸውም እንደዚያ ያሉት ሳይታወቃቸው ጭንቅላታቸው ግርጌ በተወተፈባቸው የአንድ ዘውግ ጥላቻ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር አምነውበት አይመስለኝም፡፡ በሕዝብ ይሁንታ የተቀረጸ ሕገ መንግሥት እንደሌለን እያወቁ "ሕገ መንግሥት ተጣሰ" ሲሉ ከሁሉም በፊት እርሳቸው ራሳቸው ማፈር ነበረባቸው፡፡ የሌለ ነገር ሊጣስ እንደማይችል ለአንድ ጎምቱ ዶክተር መንገር ለቀባሪ እንደማርዳት ነው፡፡

ወያኔዎች ሳይቀሩ በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት እንደሌለ ያውቃሉ – ኧረ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገርም እንደሌለች ነው የሚገነዘቡት! የምን መደባበቅ ነው – ያ እርጉም ሰውዬ ስሟን እንኳን ለመጥራት አየተጠየፈ "ሀገሪቱ" ሲል አይደለም እንዴ ዕድሜውን ጨርሶ የተገላገላት? በቀን አሥሬ "ሕገ መንግሥት፣ ሕገ መንግሥት" የሚሉት፣ "ሕገ መንግሥታችንን ሊንዱ ሲሉ … ደረስንባቸው!" የሚሉት ለማስመሰያነት እንጂ እነርሱ ራሳቸውም በዚህ ብጫቂ ወረቀት አያምኑበትም፡፡ የነሱን ሕገ መንግሥት እየጠቀሱ ለሚከራከሯቸው ታሳሪዎችና ተቃዋሚ ፖለቲከኞች "ሕገ መንግሥቱን ስኳር ግዛበት፤ እንትንህን ጥረግበት…. " እያሉ የገዛ ሕገ መንግሥታቸው ላይ በገሃድ የሚያላግጡ ባለጌዎችና ዋልጌዎች እንደነበሩ እኔ ራሴ ኅያው ምስክር ነኝ፡፡ ለዚህ ከሁሉም በላይ ወያኔና ግብረ አበሮቹ እንዳሻቸው ለሚጥሱትና ለሚንዱት የውሸት (የቁጩ) ሕገ መንግሥት ጥብቅና መቆም ዕብደት እንጂ ጤናማነት አይደለም፡፡ አህያዋ "ሳታመካኝ ብላኝ" ያለችው ወዳ አይደለም፡፡ ስለዚህ በአማራ አካባቢ በተደረጉ የድጋፍ ሠልፎች "ሕገ መንግሥት ተጣሰ" የምትሉ ወገኖች ባጭር ቃል "አማራ የዶ/ር ዐቢይን የለውጥ እንቅስቃሴ መደገፍ የለበትም" ወይም "የአማራ መነቃቃት አሳስቦናል" ብትሉ ያምርባችኋል፡፡ ግን ሃሳብ አይግባችሁ፡፡ አማራ እንደማንኛውም የኢትዮጵ ሕዝብ እጅግ ጨዋና ትሁት ነው፤ የማንም የአደጋ ሥጋት አይደለም፡፡ ላለፉት 40 ዓመታት በጥቂቶች ሲጋዝና ዘሩ እንዲጠፋ ሲደረግ አውቆ እንዳላወቀ ፍርዱን ለፈጣሪው የሰጠው እዚህ ላይ ለምገልጸው ጨዋነቱና ታጋሽነቱ ቋሚ ምስክሬ ነው፡፡ ጊዜ አገኘሁ ብሎ በሰው ላይ ክፉ የሚሠራና ቀን ሰጠኝ ብሎ በሌሎች የሚቀናጣ ሳይሆን ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው ድንቅ ሕዝብ ነው፡፡ አስፈላጊ አይደለም እንጂ ከዚህም በላይ ብገልጸው ሲያንሰው ነው፡፡

የወያኔ ሕገ መንግሥት በሕዝብ ምክክርና ውይይት የፀደቀ እንዳልሆነ ዶክተር ያውቃሉ፡፡ ሕዝብ ደግሞ የሚወደውን ከማይወደው የማይለይ ሕጻን አይደለም፡፡ አንድ ሕዝብ መብቱን በሰላማዊ ሰልፍ ሊጠይቅ ሲነሳ የሚወደውን ነገር ለማድረግ የማንንም ፈቃድ አይጠይቅም፡፡ ከመነሻው ሠልፍ የሚወጣው ተቃውሞውን ወይም ድጋፉን ለመግለጽ ነው፤ ከሕዝብ ፈቃድ ውጪ ምንም ዓይነት አስገዳጅ ነገር ሊኖር ደግሞ አይችልም፡፡ ሕዝብ የሁሉም ነገሮች የበላይ ነው፡፡ መንግሥትም የሕዝብን ፈቃድ አስፈጻሚ እንጂ ሕዝብን የሚያስር ገመድ አይደለም፡፡ በተጨማሪም ዶክተሩ የባህር ዳር ሕዝብ አማራን አይወክልም ያሉት ትልቅ ስህተት ነው፡፡ አማራን ብቻ ሣይሆን መላውን የኢትዮያ ሕዝብ የሚወክልበት አግባብም አለ – በየክልሎቹ የሚደረገውን ሰልፍ ማየትም ይቻላል፤ ሴትዮዋ "ዕድሌ ሆኖ ፈሴ ይሸታል"

እንዳለችው ሆኖ እንጂ እነዶክተር አማራን የከሰሱበት ንጹሕ የኢትዮጵያ ባንዲራ ለዚያውም ከባህር ዳር ዕጥፍ ድርብ በሚበልጥ ሁኔታ በሌሎች ሥፍራዎችም ተውለብልቧል፡፡ ያ የባህር ዳር ሰልፍ ኢትዮጵያን ቀርቶ አማራን አይወክልም ስለተባለው ደግሞ በጥናታዊ ወረቀት የሳምፕሊንግ መጠን ሬሽዎን ብናይ የሚጠናው ነገር ቁጥሩ ከአሥር ሺህ በላይ ከሆነ አሥር መቶኛው በሳምፕሉ ቢካተት አጥጋቢ ውጤት እንደሚገኝ ይነገራልና ከዚህ አኳያ የባህር ዳርና አካባቢዋ ሕዝብ ባካሄደው ሰልፍ ሁለት ሚሊዮን ገደማ ሕዝብ ቢገኝ ቢያንስ የአማራን ሕዝብ ስሜት እንደሚወክል መገመት አይከብድም፡፡ ለነገሩ የባሕር ዳር ሕዝብ የራሱን እንጂ የሌሎች አማሮችንም ሆነ ኦሮሞዎች ስሜት እወክላለሁ ብሎ ሰልፍ አልወጣም፡፡ ችግሩ የአመለካከት ጉዳይ ነው፡፡ እነዶ/ር ነጋሦ በአማራው ላይ የተንሻፈፈ አመለካከት ካላቸው አይጠቅምምና ቢስተካከሉ ለሕዝባችን የአብሮነት ሕይወት ትልቅ አስተዋፅዖ አለው፡፡ የቆዬ እውነተኛም ይሁን ምናባዊ ቁስል እያነፈረቁ የአዲሱን ዘመን ወጣቶች ሕይወት ለማበላሸት መሞከር በተለይ ልጡ ከተራሰ ጉድጓዱ ከተማሰ ሰው አይጠበቅም ብቻ ሣይሆን ነውርም ነው፡፡የራስን ሕይወት በግጭትና በጭቅጭቅ እንደነገሩ አገባዶ የሌሎችንም ሕይወት በተመሳሳይ ቅኝት ለማጨለም መሞከር ዛሬ ባይሆን ነገ በታሪክ ያስጠይቃል፡፡ ትምርትና ሽበትስ ለመቼ ሊሆኑ?

እነ ዶ/ር ፀጋየ ምን ቤት እንደሆኑ ሊገባኝ አልቻለም፡፡ በአንድ የቅርብ ጊዜ ቃለ ምልልሳቸው እንደሸሮ ከላይ ከላይ ሲንደቀደቁ ሰማሁና በጣም ገረመኝ፡፡ እነዚህ ወጣቶችና ጎልማሦች ለውጥን አይፈልጉም፡፡ ሀገር እየታመሰች በመኖሯ ትርፍ የሚያገኙ ይመስለኛል፡፡ ምቹ ቦታ ተቀምጦ በእሾህና በአሜከላ ላይ በተቀመጠ ሕዝብ የፖለቲካ ቁማር መቆመር ቢያንስ ትዝብት ውስጥ እንደሚከት የተገነዘቡ አልመሰለኝም፡፡ ሀገር ለውጥ እንደሚያስፈልጋት ሲደሰኩሩ ከርመው አሁን ለውጡ ሲመጣ የለውጡ አቅጣጫ እነሱ እንደሚፈልጉት ከነሱው ጎራ ባለመምጣቱ ይመስላል ይህን አገር ምድርን እያናወጠ የሚገኝ ለውጥ ሲያንቋሽሹ ይስተዋላል – በትንሹ ብልግና ነው፡፡ እነዚህን ዓይነቶቹን በራሳቸው የተጣመመ ዓለም ውስጥ ለሚዳክሩ ሰዎች “ኢይጥዕም መዓር ለአድግ ዘእንበለ እንጉስታር” የሚለው ግዕዛዊ ብሂል በግሩም ሁኔታ ይገልጻቸዋል – “ለአህያ ማር አይጥማትም” ለማለት ነው፤ አካሄዳቸው ሁሉ ከሰው አይገጥምም – “ያውጡብሽ እምቢ፣ ያግቡብሽ እምቢ” ዓይነቶች፡፡ የሀበሻን የምቀኝነት አባዜ ያስታውሰናል የነዚህ ሰዎች ነገር፡፡ በዚያን ሰሞን አንዱ የለየለት ምቀኛ አብሮ ሯጩን የሀገሩን ልጅ እንዳይቀድመው በማሰብ ጎትቶ ሲያስቀረው አይተናል፡፡ ጥሩ የሀገራችን መገለጫ ነው፤ እጅግ አፍሬያለሁ እኔ፡፡ በዓለም ጉድ እንድንባል ያደረገ ክስተት ነበር፡፡ እነፀጋየም ከዚሁ ባልተናነሰ ዓለምን ጉድ ያሰኘ የለውጥ እንቅስቃሴ ለምን በዘረኝነት መርዝ አልታሸም በሚል የዶ/ር ዐቢይን የለውጥ ጅምር ሲያራክሱ ሰማን፡፡ ይባስ ብለውም የነዐቢይን መግነንና የነሱን መቀዛቀዝ በሚመለከት ሲጠየቁ “because we are here; they are there” በማለት ቅንጣት ሳያፍሩ ተናገሩ፡፡ በዚህም ስለነሱ በጣም አፈርኩ፤ እጅግም ገረመኝ፡፡ ነገሩ ሁሉ ቅናት ነው፡፡ ቅናት መጥፎ ነው፡፡ አቤል የመጀመሪያውን ሰብአዊ ሞት የሞተው በቅናት በተመረዘው በወንድሙ ቃየል አማካይነት ነው፡፡ የነዶ/ር ዐቢይ ስኬት እነዶ/ር ሄኖክን ማበሳጨት አልነበረበትም – ማስደሰት እንጂ፡፡ ዶ/ር ፀጋየ በዚያ ሁኔታ እርር ድብን ሲል መታየት አልነበረበትም – በደስታ ጮቤ መርገጥ እንጂ፡፡ አንዱ ፓንትን እየሳበ ከሩጫ ያደናቅፋል – ሌላው በመራራ የምቀኝነት ንግግሩ የከፉ ቀን ደራሽ ልጆቻችንን በሕዝብ ሊያስጠላ ይዳክራል፡፡ ኦኤምኤን ከዚህ ዓይነት አፍራሽ ድርጊቱ ቢቆጠብ ተጠቃሚው ሰፊው የኦሮሞና ሌላውም የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው፡፡ ሞኝ ሰው የጋራ ቤቱን ያፈርሳል፤ ብልኅ ሰው የተሸነቋቆረ የጋራ ቤቱን በኅብረት ያድሳል፡፡ ምርጫው ለሁላችንም ነው፡፡ ዋናው መታወቅ ያለበት ነገር ሕዝቡ ዕብድንም ጨዋንም በደንብ ይለያል፡፡

የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ሕዝቡ የሚመርጠውና የሚያውለበልበው እንጂ እነዶ/ር ነጋሦ ከሕዝብ ዕይታና ፈቃድ ውጭ ሆነው በዝግ የውሸት ፓርላማ የወሰኑለት ሊሆን አይችልም፡፡ ሕዝብ “ባንዲራየ ጥቁርና ግራጫ ነው” ቢል መብቱ ነው፡፡ ማንም ሊወስንለት አይገባም፡፡ የሀገራችን ሕዝብ በአብዛኛው እያውለበለበ የሚገኘው አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀዩን ልሙጥ ባንዲራ ነው፡፡ ይህን ፍላጎት አዲሱ የለውጥ አራማጅ ኃይል ተገንዝቦ በአስቸኳይ ማስተካከያ ሊሰጥበት ይገባል፡፡ የሌባና ፖሊስ ጨዋታው ማክተም አለበት፡፡ ወያኔያዊው እልህ የመጋባትና በእልህ አገርን የመግዛት አባዜ ዛሬውኑ ሊቆም ይገባል፡፡

የሕዝብን ፍላጎት ማክበር የዴሞክራሲያዊ አስተዳደር መሠረት ነው፡፡ የወሮበላው የወያኔ ቡድን ከእንግዲህ ፍላጎቱን በሕዝብ የሚጭንበት አንድም ምክንያት ሊኖር አይገባም፡፡ የሕዝብ ፍላጎት እንጂ የጠባብ ቡድኖች ፍላጎት ገዢ ሆኖ መቀጠል የለበትም፡፡ ሕዝብ እየሞተና እየተሰቃዬ የሚገኘው ለወያኔ ጥፍጥፍ ባንዲራ ሳይሆን ቀደምት አባቶችና እናቶች ዘርና ሃይማኖት ሳይለያያቸው ለድንበራቸውና ለሀገራቸው ባንድ ላይ ሲዋደቁ ላውለበለቧት ንጹሕ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ የኢትዮጵያ ባንዲራ ነው፡፡ ባንዲራ ደግሞ ሸሚዝና ከናቴራ አይደለም፡፡ መንግሥት በመጣና በሄደ ቁጥር ባንዲራና የሕዝብ መዝሙር ስንቀያይር መኖር የለብንም፡፡ እንደግ፡፡ ዐቢይን እንከተለውና እንብሰል፡፡ አድሮ ጥሬ ከመሆን በአፋጣኝ እንውጣ፡፡ ከሌሎች ሀገራትም ትምህርት እንቅሰም፡፡ ባለንበት መርገጥን እንጠየፍ፡፡

ከኤርትራ ጋር የተጀመረው ዕርቅና ስምምነት እጅግ ግሩም ነው፡፡ ይህ ጅምር እንዲጎለብት ሁሉም የድርሻውን ይወጣ፡፡ ቀድሞውንም ሁለት ሀገራት የሆኑት በሕዝብ ምርጫ ሳይሆን በግለሰቦች ምርጫ ነው – ያለፈ አልፏል፤ “ላለፈ ክረምት ቤት አይሠራም”ና ይሁን፡፡ ጊዜ ይለወጣል፡፡ ታሪክ ይቀየራል፡፡ ይህ ጊዜ ከፈጣሪ ዘንድ የተላከ እንደመሆኑ በመጪው ዘመን ሁለቱ ወንድማማች ሕዝቦች የተለዬ ታሪክ ሊሠሩ ይችላሉ፡፡ የታሪክንና የፈጣሪን ፍርድ መጠበቅ ነው፡፡ ለማሰናከል ግን መሞከር የለብንም፡፡ በፈረስ የማያገኙት ዕድል ይህን ብላቴና ተመስሎ ከፈጣሪ ደርሶልናልና ዕድሉን በጸሎትም በሥራም እንጠብቀው፡፡

ወያኔዎች ይህን ለውጥ ለማጨናገፍ የማይቆፍሩት ጉድጓድና የማይበጥሱት ቅጠል የለም፡፡ የፈጣሪን ትዕዛዝ የሚያስተጓጉል ባይኖርም ከኛ ጉድለት እንዳይታይ መትጋት ይገባናል፡፡ የግል ፍላጎት ማለቂያ የለውም፡፡ የግል ሥልጣን ሱስ ገደብ የለውም፡፡ የግል የሀብት ክብረት ፍላጎት ድንበር የለውም፡፡ እነዚህን መሰል ወሰን የለሽ ግላዊ ፍላጎቶች የሚያሰቃዩን ዜጎች እንደምንም እየታገስንና ከተቻለ በባህላዊም ሆነ በዘመናዊ ህክምና እየተረዳን የነዚህን ልጆች የለውጥ እንቅስቃሴ እንደግፍ – ለኛው ለራሳችንና ለልጆቻችን ስንል፡፡ ቢያንስ ከማደናቀፍ እንቆጠብ፡፡ በልቶ ለማይጠረቃ ሆድ፣ ለብሶ ለማያምርበት ሰውነት፣ ገንኖ ለማይጠገብ የሥልጣን ሱስ ስንል መልካም ጅምሮችን ለማጨናገፍ አንሞክር፡፡

በዚህን ወቅት “የሽግግር መንግሥት ይመሥረት” የምትሉ ቅንጡዎች ደግሞ ዕረፉ! ምን ዓይነት አስተሳሰብ እንደሆነ ሊገባኝ አይችልም፡፡ ይህን ነገር የሚያነሣ አንድም ኢትዮጵያንና አሁን ያለችበትን አሳሳቢ ሁኔታ አያውቅም አለበለዚያም በሥልጣን ሱስ ናውዟል፡፡ እየተካሄደ ያለው ለውጥ በአንድ የሽግግር መንግሥት ምርጫም አይደለም በሙቶ የቋሚ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ምርጫም ሊታይ የሚችል አይደለም፡፡ የሽግግር መንግሥት ይቋቋም የሚሉ ወገኖች ዘበናዮች ናቸው፡፡ ራሳችንን እያሳከከን እግራችንን ሊያኩልን የሚቃጡ የፈረንሣይዋ ልዕልት ዓይት ሞልቃቆች ናቸው፡፡ እንደእውነቱ ሃሳቡን ጠልቼው አይደለም፤ ግን ጊዜው አይደለም፡፡ (አንድ የትግራይ ኮሚክ ሰው እንዲህ አለ አሉ – እሁድ ቀን ነው፡፡ በጧት ወደ ቤተ ክርስያን እየሄደ ነው፡፡ አንድ ጓደኛው መንገድ ላይ ያገኘውና ‹ና ቁርጥ ሥጋ ልጋብዝህ› ይለዋል፡፡ ቀልደኛው ሰውዬ ወደሚሄድባት የቅ. ማርያም ቤተ ክርስቲያን ዞር ይልና በትዕምርተ መስቀል ሰላምታ በማቅረብ ‹ቧይ! የማስቸግርሽስ ለዚህ አይደለም እንዴ እመ ብርሃን?!› በማለት ቅዳሴውን ትቶ ወደ ቁርጡ አመራ፡፡” ) እኛስ የምንፈልገው በቅድሚያ የመቀመጫችን ወያኔያዊ እሾ እንዲነቀልልን አይደለም እንዴ ጎበዝ! አንድ ሳይባል ሙቶም ሆነ ሽህ አይባልምና የያዝነውን ዕድል ላለማጣት እያስተዋልን እንራመድ፡፡ ሁሉም በጊዜው ይደርሳል፡፡

በመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና በወረዳና ከፍተኛ እንዲሁም በማዘጋጃ ቤቶች አካባቢ ያላችሁ ሰዎች ተጠንቀቁ፡፡ የኑሮ ግሽበት እንዲፈጠር እያደረጋችሁ ያላችሁ የሕወሓት ደጋፊ ነጋዴዎችና አስመጭና ላኪዎችም ወደኅሊናችሁ ተመለሱ፡፡ “አገባሻለሁ ያለ ላያገባሽ ከባልሽ ሆድ አትባባሽ” እንዲሉ ከማያዛልቃችሁ ፈራሽ ሥርዓት ጋር በመተባበር ታሪካችሁን አታጉድፉ፡፡ ይብላኝ ለእናንተ እንጂ ሁሉ ነገር ነገና ከነገ ወዲያ ይስተካከላል፡፡ ኢትዮጵያ ካለእናንተ መኖር የምትችልበትን ዕድል በአፋጣኝ ታመቻቻለችና በምትሠሩት የጅል ሥራ አትደሰቱ፡፡ ሁላችሁም የምትሠሩት እያንዳንዱ የኢኮኖሚና የአስተዳደር ሻጥር ይታወቃል፤ አሁን በደስታ የምንኖረው በእናንተ የተቀነባበረ አሻጥር ሳንከፋ ቀርተን ወይም እነዐቢይ ፍላጎቶቻችንን አሟልተውልን ሣይሆን ነገን እያሰብን ነው – ወደ እናንተ መዞር በጣም

ቀላል ነው፡፡ “በብርጭቆ ቤት ውስጥ የሚኖር ድንጋይ ለመወርወር የመጀመሪያው መሆን የለበትም” የሚለውን የደርግ ማስጠንቀቂያ አስታውሱ – ነገ ከማልቀስ ዛሬ አንጎላችሁን አሠሩት፡፡ የሕዝብ ዐይኖች 24 ሰዓት ክፍት ናቸው፡፡ ለውጡን በመጠራጠር ወይም በተዘፈቃችሁበት የሙስና ወንጀል በመጥበርበር ይህን ለውጥ ለማደናቀፍ ከወያኔ ጋር ብትዋሸሙ መጨረሻችሁ አያምርም፡፡ ይልቁንስ ንስሃ እየገባችሁና ለሠራችሁት ወንጀልና በደል እየተጸጸታችሁ ወደ ለውጡ መርከብ በአፋጣኝ ግቡ – ወንድማዊ ምክሬ ነው፡፡ እናንተም ልክ እንደወያኔ ሁሉ ጊዜ የላችሁም፡፡ ይህ የለውጥ ማዕበል በምንም ዓይነት መንገድ የሚጨናጎል አይደለም፡፡ ነገ ወያኔ ተመልሶ ያድነኛል የምትሉት ነገር የለም፡፡ አብቅቷል፡ ፡ ይልቁንስ ሚናችሁን ለዩ፡፡ ከሟች ጋር ለመሞት ከቆረጣችሁ መፃዒ ዕድላችሁን በቅርቡ ታያላችሁ፡፡ ምላሤ ጥቁር ነው – ጠብቁ!

ወያኔዎች ቀናችሁ አልቋል፡፡ “ከመነሻችሁ ጀምሬ ስምክራችሁ ነበር”፤ እንተዋወቃለን፡፡ አወዳደቃችሁን ሣይቀር እነግራችሁ ነበር፡፡ ከሰው የሰማሁትንና ከመጻሕፍት ያነበብኩትን በመጥቀስ አንድ ቀን ጀምበራችሁ እንደምትጠልቅ እናገርና እጽፍ ነበር – የምላችሁ ሁሉ ለማንም የማይቀር ቢሆንም አስተውላችሁ ብትራመዱ መጨረሻሁ ያምር እንደነበር ከጥንት ከጧት ጀምሬ ሳልጠቁማችሁ አልቀረሁም፡፡ ያ ጊዜ ሳልሞት ደረሰ፡፡ በጉልኅ እያየሁት ነው፡፡ ከ27 ዓመታት በፊት በጠበንጃና በአሻጥር እንዲሁም የሕዝብ ብሶት በደርግ መንግሥት ላይ በወለደው ኩርፊያና በጥንቆላ እንደገባችሁ አሁን ደግሞ በፍቅር ጦር ተወግታችሁ አራት ኪሎን እስከወዲያኛው ልትለቁ ነው፡፡ ምንም ብታደርጉ አትተርፉም፡፡ ምክንያቱም ጊዜው የሌላ ነው፡፡ የጊዜን፣ የፈጣሪንና የታሪክን ፍርድ እንኳን እናንተ ማይማኑ ብዙ የተማረ ኃይል ከጎናቸው ያሠለፉት እነሂትለርና ሙሶሊኒም አልቻሉትም፡፡ ስለዚህ ለእናንተም ሆነ እንወክለዋለን ለምትሉት የትግራይ ሕዝብ ፈተና አትደቅኑበት፡፡ የመንታ እናት ተንጋላ ታጠባለች፡፡ ላምም እሳት ትወልድና እንዳታጠባው እሳት ይሆንባታል – እንዳትተወውም ልጇ ነውና በሁለት አጣብቂኞች ተሰንቅራ ትሰቃያለች፤ ለዚህ ሁሉ ውጥንቅጥ ችግር መንስኤዎቹ እናንተ እንደሆናችሁ ሁሉ የመፍትሔ እርምጃውም ያለው በእናንተው እጅ ውስጥ ነው – ጊዜ ደግሞ የላችሁም፤ ተጣደፉ፡፡ ላለቀ ነገር መፍጨርጨር ያለቀን ነገር ማንዘላዘል ካልሆነ እስትንፋሱን አይቀጥልም፡፡ የሞኝ ሥራችሁን አሁኑኑ ተውት፡፡ ጥሩ ሰው አግኝታችኋል፡፡ ዶ/ር ዐቢይ ጥሩ የነፃነት አርበኛችሁ ነው፡፡ እርሱን አስወግዳችሁ ሌላ ሰው ከተካው ውርድ ከራስ ቦታውን እናንተ በጭራሽ አትይዙትምና በራሳችሁ ላይ እቶን እሳት አነደዳችሁ ማለት ነው፡፡ ባለፈ ታሪክ የሚኖር የለም፡፡ ያለፈ ኃይለኝነት ለዛሬ አይሠራም፡፡ በምናብ ጦርነት ጠላቱን ያሸነፈም የለም፡፡ እንዲህ የምትፍጨረጨሩት የኢትዮጵያን ወቅታዊ ሁኔታ እንደኔ በግልጽ ባታዩት ነው፡፡ የዞረባችሁ ነገር አለና ፈልጉት፡፡ እናም ይልቁንስ ለውጡንና የለውጥ ኃይሎችን ለመግደል ከማጥመድና አምና ለኮብል ስቶን ያጫችኋቸውን የዩንቨርስቲ ምሩቃን ዘንድሮ ለቦምብ ጣይነት እያሠለጠናችሁ አገርን ለማተረማመስ ከምትፍጨረጨሩ ወደ ልቦናችሁ ተመለሱ፡፡ የባል ውሽማ ደግሞ አይሆንም – ነውር ነው፡፡ ያን ሁሉ መትረየስና ሚሣይል የተቆጣጠራችሁ ሰዎች ዛሬ የወረዳ ወርዳችሁ እዚህና እዚያ ቦምብ ስትወረውሩ ስትታዩ ለታሪካችሁና ለውጭ ታዛቢም በጎ አይደለም፡፡ በቃ፡፡ ሲያልቅ አለቀ ነው፡፡ አስተላለቅን መረዳትና እንደጊዜና ሁኔታው ራስን ማሰተካከል ግን ብልኅነት ነው፡፡ እናም ዐቢይን ጠብቁት – ለእናንተና ለትግራይ ስትሉ፡፡ ጨረስኩ፡፡